# ሽሮ ተወደስ

አደራህን ሽሮ ጉድ እንዳታደርገን፣
ካበደ ጋር አብደህ እንዳታሳብደን።
በርበሬ ሲወደድ ሲቃጠል ስትሰማ፣
እንዳትጠፋብን አንተም ከከተማ።
አሁንም አደራ ያለ ግብርህ ገብተህ፣
እሣት እንዳትሆን ከእሣት ጋር አብረህ።
ያ ገበታ አድማቂ ኮስታራው አጅሬ፣
«ማን እንደኔ» ብሎ የኮራው በርበሬ፣
ግብሩ መፋጀት ነው ይኼን እናውቃለን፣
ሲጠፋ ባሰበት ይበልጥ አቃጠለን።

አንተ እና በርበሬ ኅብረት ነበራችሁ፣
ሚሊኒየም መጥቶ ጠብ ሳይዘራባችሁ።
ወፍጮ ቤት ይታዘብ ያለው እስከ ዛሬ፣
ተነጥሎ ሲቀር ከአንተ ጋር በርበሬ።
ታሪክ ምስክር ነው አይክድም ላንዳፍታ፣
ቃሪያ ችሎ አይተካው የበርበሬን ቦታ።
ዘንድሮ ቢኮራም ካለው ጋር አብሮ፣
በርበሬ አይተካውም የአንተን ቦታ ሽሮ፣
ደጋግመህ ተወደስ ተሰፋችን አንተ ነህ፣
ሽሮ ከበርበሬ እጅግ ትበልጣለህ፣

የበርበሬ አፋኞች አንተንም አፍነው፣
ዋጋህን ሊያበዙት «ረክሰኻል» ብለው።
አንተንም መርካቶ ቢደብቁህ ወስደው፣
ኡኡ! እንድትል ሽሮ ፊት እንዳትሰጣቸው።
አዲስ ወግ አምጥቶ ከትናንቱ ዛሬ፣
«ተወደድኩኝ» ብሎ ተጠልቷል በርበሬ።
በጭራሽ እንዳታልፍ በበርበሬ መንገድ
መወደድ ከፈለክ ሽሮ እንዳትወደድ።
በአንተ ከመጡብን ዝም አንልም ከቶ፣
«ጃን ሜዳ» ይሆናል ይፈርሳል «መርካቶ»።

አብርሃም ሰሎሞን
ጥቅምት ፲፬/፳፻ ዓ.ም.
ሚኒሶታ